بسم الله الرحمن الرحيم

**የድጋፍ መግለጫ**

**ለፈርስት ሂጅራ ፋውንዴሽን ዋሽንግተን ዲ.ሲ.**

ጉዳዩ፦ All Ethiopian Muslims Day of Protest on 20 th of march 2009

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መብት እንዲከበርና ጭቆና ይቆም ዘንድ እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ የዜጎች እኩልነት እውን እንዲሆን ለሰላም የምታደርጉት ያላሰለሰ ጥረት አላሁ ስብሃነሁ ወተዓላ ምንዳችሁን እንዲከፍላችሁ ዱዓ እያደረግን የኢትዮጵያ ዑመትን የመብት ጥያቄ ወደ አደባባይ በማውጣት ለጠራችሁት ሰላማዊ ሰልፍ ከጎናችሁ በመሆን የሚቻለንን ሁሉ የምናደርግ መሆናችንን ልንገልጽላችሁ እንወዳለን።

ይህ አንጋፋ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊም ድርጅታችሁ የዛሬ 14 አመት ተወዳጁ አባታችን ሃጂ መሐመድ አህመድ ወሌን(አላህ ይርኸማቸው) የመሰሉ ታዋቂ ዓሊሞቻችንና አባቶችን በዚሁ መንግስት የኃይማኖት ጣልቃ ገብነት ወደ እስር ቤት በተወረወሩበት ጊዜ ያደረጋችሁትን ጥረት ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ ከአምኒስቲ ኢንተርናሽናል ከአሜሪካ መንግስት ባለስልጣናት ከኢትዮጵያ መንግስት በጊዜው ከፓርላማ አፈ-ጉባዬና በመጨረሻም ጠቅላይ ሚንስትሩን በአካል ያነጋገራችሁበትንና እኛም በአውሮፓ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የአባቶቻችን የእስራት ዘመን እንዲያጥርና ባስቸኳይ እንዲፈቱ ያደረግንበትን ጊዜ በማስታወስ ነው።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 14 ዓመታት ያሉትን ሁኔታዎችና ያደረጋችሁትን የትግል አስተዋጽዖ ሁላችንም በጋራ የምናውቀው ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ አንገባም። ዋናው ቁምነገር ግን የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ መሪ ድርጅት የሌለው በገዛ ሃገሩ የበላይ ተመልካች ሆኖ መቀጠል ስለማይችል ለመብቱና ለነጻነቱ ለሰላም ድምጹን ከማሰማትና ከመታገስ ወደኋላ ማለት ታሪክ የማይረሳው ታላቅ ስህተት ነው። በተለይ ይባስ ተብሎ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ ያነጣጠረው ተከታታይ ሴራ(በደል) የመጨረሻ ደረጃው የደረሰበትና እምነቱ በአደባባይ በአክራሪዎች የሚሰደብበት፣ አገር ለቃችሁ ውጡ የሚባልበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ይህ ለሀገርና ለህዝቡ መርዝ የሆነ የአክራሪዎች ሂደት በአስቸኳይ መገታት ይኖርበታል፥ ካልሆነ አደጋው ከፍተኛ ነው ብለን እናምናለን። ስለሆነም ድምጽን ከፍ አድርጎ አደባባይ በመውጣት ጉዳዩን ለአለም አቀፉ ሚድያ በማድርስ ለሃገሪቱ የእስልምናና የክርስትና እንዲሁም የመንግስት አካላት ግልጽ የሆነ የሰላም ጥሪ መደረጉ እጅግ በጣም ወቅታዊና አስፈላጊ ነው።

የተከበራችሁ ወንድምና እህት የፈርስት ሂጅራ አመራር አካላት፦ ይዛችኋቸው የምትወጡትን መፈክሮች በአጠቃላይ በመደገፍ እነዚህ ከታች የምንጠቅሳቸው ነጥቦችም እንድታክሉባቸው በአክብሮት እንጠይቃለን።

1. አክራሪነትን በሁሉም የእምነት እምነት እንቃወማለን
2. ሴኩላሪዝም በተግባር ይገለጽ
3. የጊዮርጊሱ ጽንፈኛ ሰባኪና ሌሎችም በተለያዩ መንገዶች ሙስሊሙ ላይ በእምነቱና በሃገራዊ ማንነቱ ላይ ያፌዙ በአስቸኳይ ለፍርድ ይቅረቡ
4. መጅሊሱ አሁንም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የሚያስተዳድሩት ነጻ ተቀዋም እንዲሆንና መንግስት እጁን ያውጣ የሚሉ ናቸው።

እንዲሁም ለኢትዮጵያ መንግስት የሚላከውን ደብዳቤ ኮፒ በአውሮፓ፣ በአፍሪካና በእስያ ለሚገኙ አምባሳደሮቻችን ይደርሳቸው ዘንድ ጥረት እናደርጋለንና የደብዳቤውን ኮፒ እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን።

የኔትዎርኩ አባላትና በአውሮፓ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሕገ-መንግስቱ ተከብሮ የኢትዮጵያ

ሕዝብ ሰላም አግኝቶ ብልጽግና እድገት ብሎም ፍትህ እዉን እንዲሆን ትግላችንን አለ በተባለው መንገድ ከማካሄድ ወደኋላ የማንል መሆናችንን ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን።

ጀዛኩሙላህ ኸይረን

በአውሮፓ የኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞች ኔት ወርክ

March 13.2009